# ፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምፅ

## Finote Democracy Voice of Ethiopian Unity

efdpu@aol.com www. Finote.org

**ፕሮግራም፡-** ረቡዕና እሁድ ከምሽቱ ሁለት ሰዓት እስከ ሶስት ሰዓት በ 25 ሜትር ባንድ

**Program**: Wednesday and Sunday 8:00PM- 9:00 PM on 25 meter band.

## <u>ዜና ዘገባ</u>

**ጥር 12 ቀን 2004 ዓ.ም**

**የጋምቤላ ክልል የባለስልጣናት ግምገማ ብዙ ምስጢሮችን አጋለጠ፤**

**በ1996 ዓ.ም በአኙዋክ ብሔር ተወላጆች ላይ ጅምላ ጭፍጨፋ እንዲፈጸም ያዘዘው መለስ ዜናዊ መሆኑን የገዛ ካድሬዎቹ አጋለጡ፤**

**የጋምቤላ ክልል ፕሬዝዳንት ከስልጣኑ በተባረረ በ24 ሰዓት ውስጥ ተመልሶ ተሾመ፤**

**አፋር ውስጥም እሳት መንደድ ጀመረ፤**

**ሶስት ከፍተኛ የአፋር ክልል ባለስልጣናት ተጠልፈው ታሰሩ፤**

**ርሀብ በአዲስ አበባ ተስፋፍቶ ቀጥሎዋል፤**

የወያኔው ቁንጮ መለስ ዜናዊ አራት ኪሎ ቤተ መንግስት ከገባበት ግዜ ጀምሮ ባለስልጣናቱን እያመሰና እያተራመሰ..... እርስ በርስ እያጋጨ...... ብሎም እየቀለደባቸው የነበረ ሲሆን አሁን ደግሞ እየወነጀላቸው ከስልጣናቸው እያባረረ ለእስር እየዳረጋቸው መሆኑ ታወቀ።

በኦሮሚያ ክልል ባለስልጣናት ላይ ሲጫወትባቸው የቆየው መለስ ዜናዊ ሰሞኑን ደግሞ የጋምቤላና የአፋር ክልል ባለስልጣናትን እያስለቀሰ እና እያሰቃያቸው መሆኑ ታውቆዋል።

ለአንድ ሳምንት በቆየው ግምገማ ላይ የጋምቤላ ክልል ባለስልጣናት ሲታመሱ የሰነበቱ ከመሆኑም በላይ መለስ ዜናዊን ጨምሮ የወያኔ ባለስልጣናት በሀገር እና በህዝብ ላይ ሲፈጽሙዋቸው የነበሩትን ግፍ እና በደል ሲያጋልጥ ወንጀለኞች መሆናቸውን ሲያረጋግጥ የነበረ መሆኑንም ከስፍራው የደረሰን ዘገባ ገልፆዋል።

ከጠቅላይ ሚኒስትር ቢሮ በተላኩ ከፍተኛ ባለስልጣናት ገምጋሚነት ሲደረግ የቆየው ይሄው የጋምቤላ ክልል ባለስልጣናት ግምገማው እጅግ አስገራሚ ምስጢሮችን ሲያጋልጥ መሰንበቱንም ከቦታው የደረሰን ዘገባ አጋልጦዋል።

የወያኔ አጋር የሆነው የጋምቤላ ህዝብ አንድነት ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ ድርጅት መሪዎች ከ9 ዓመት በላይ በስልጣናቸው ላይ የቆዩ ቢሆንም እያደር በወያኔ ላይ በሚያቀርቡት ቅሬታና ተቃውሞ የተነሳ ጥርጣሬ የገባው መለስ ዜናዊ በክልሉ ባለስልጣናት ላይ ግምገማ እንዲደረግ ባዘዘው መሰረት ሰሞኑን ለሰባት ቀናት የፈጀ ግምገማ ቢደረግም የግምገማው ውጤት ግን መለስን ጨምሮ ሌሎች ባለስልጣናትን ወንጀለኞች መሆናቸውን አረጋግጦ የቁዋጨ መሆኑ ታውቆዋል፡፡

የጋምቤላ ክልልን እና ጋህዴንን ለ9 ዓመታት የመለስ ቀኝ እጅ ሆኖ ሲመራ የቆየው ኦሞት ኦቦንግ ኦሎም ሰሞኑን በተደረገው ግምገማ ላይ በ1996 ዓ.ም የተፈጸመውን የጅምላ ጭፍጨፋ እንዲያምንና እንዲያጋልጥ በመደረጉ መለስ ዜናዊ ዋነኛ ተጠያቂ መሆኑን ጨምሮ ማጋለጡን ከስፍራው የደረሰን ዘገባ አጋልጦዋል፡፡

የወያኔ ተለጣፊ አባል የሆነው ጋህዴን አመራሮች ባደረጉት በዚሁ ግምገማ ላይ ብዙ ትችቶች እና ውግዘቶች ቢደርስባቸውም ያለ አንዳች ፍርሀት እና ይሉኝታ አፀፋዊ ምላሽ በነመለስ ዜናዊ ላይ የሰላ ትችት እና ወቀሳ ሲሰነዝሩ መሰንበታቸውንም ከስፍራው የደረሰን ዘገባ አስረድቶዋል፡፡

የህግ የበላይነትን አታከብሩም..... እርስ በርስ ግጭት እንዲፈጠር ታደርጋላችሁ..... ከባለሀብቶች ጋር ትሞዳሞዳላችሁ.....በሚል ሰሞኑን ውጥረት የተሞላበት ግምገማ ያደረጉት የጋምቤላ ክልል ባለስልጣናት ዋነኛ ተጠያቂው እኛ ሳንሆን እነ መለስ ዜናዊ ናቸው በማለትም በይፋ ሲናገሩ መደመጣቸው ታውቆዋል፡፡

የመንግስት እና የፓርቲ ስልጣን ተለይቶ ባልታወቀበት በወያኔ ቡድን ውስጥ ተለጣፊ የሆነው የጋህዴን አመራሮችም ሰሞኑን በተደረገ ግምገማ ከስራ አስፈጻሚነታቸው ብዙዎቹ መባረራቸውንም ይሄው የደረሰን ዘገባ ገልፆዋል፡፡

የፓርቲው ባለስልጣናት ከኃላፊነታቸው እንዲነሱ የተወሰነው ለአንድ ሳምንት በዘለቀው የወያኔ የስራ እንቅስቃሴ ግምገማ ላይ ሲሆን በዚሁ ግምገማ ላይ አበይት ሆኖ የተነሱት አጀንዳዎች በሙስና መዘፈቅ.....ግዙፍ የእርሻ መሬቶችን ለባዕዳን ኢንቨስተሮች መሸጥ.....በ1996 ዓ.ም በአኝዋክ በሔር ላይ የጅምላ ጭፍጨፋ መደረጉን......እንዳጠቃለለ ለማወቅ ተችሎዋል፡፡

በተለይ በ1996 ዓ.ም በተደረገው የግፍ የጅምላ ጭፍጨፋ ላይ በወቅቱ የጋምቤላ ክልል ፖሊስ ኮሚሽን የነበረው የአሁኑ ፕሬዝዳንት ኡሞድ ኡቦንግ ኦሎም እንደነበረ የጠቀሰው የግምገማ ውጤት ለተፈጸመው ጅምላ ጭፍጨፋ ወንጀለኛ እንደነበር እራሱ ያጋለጠ ከመሆኑም በላይ እኔ በወንጀል የምጠየቅ ከሆነ መለሰ ዜናዊ ቅድሚያ ሊጠየቅ ይገባል በማለት አጽንኦት ሰጥቶ መግለፁም ታውቆዋል፡፡፡

በወቅቱ ሲፈፀም የነበረውን ጨፍጨፋ አስመልክቶ ሲያብራራም በዚያን ግዜ እኔ የፖሊስ አዛዥ ሆኜ ስሰራ እርስ በርስ ጥቂት ግጭቶች ነበሩ ቢሆንም ነገሩን በሽምግልና ለመጨረስ እየተንቀሳቀስን ሳለ ድንገት አንድ ሻለቃ ጦር በከፍተኛ መኮኑን ሻለቃ ገብረእግዚያብሔር በተባለ ግለሰብ የሚመራ መጥቶ ሌሊቱን በአኙዋኮች ላይ እርምጃ እንዲወስድ ተደረገ ያለው የአሁኑ ፕሬዝዳንት ኡቦንግ ከመለስ ዜናዊ የመጣ ትዕዛዝ ነው ተብዬ እነሱን እንዳግዛቸውና የጉዳዩ ተዋናይ እንድሆን ታዝዣለሁ ሲልም ማብራሪያ ሰጥቶዋል፡፡

እኔን እና በወቅቱ የክልሉ ፕሬዝዳንት የነበረውን ኦኬሎ አኩዋይን በበላይነት እንዲቆጣጠሩና እንዲያስፈጽሙ የተላኩት ሁለት የህወሀት ከፍተኛ ባለስልጣናት ነበሩ ያለው ይሄው የወያኔ ተላላኪና ጉዳይ አስፈጻሚ ግለሰብ በተለይ ዶክተር ባርናባስ የተባለው የፌዴራል ጉዳዮች ሚኒስትር ደኤታ የነበረውና ጦሩን የሚመራው ሻለቃ ገብረእግዚአበሄር የተባሉት ሁለት ሰዎች የመለስን ተዕዛዝ ሲያስፈጽሙ የነበረ መሆኑን አጋልጦ በመጨረሻም ሁኔታው አላምር ሲላቸው እኔን የጉዳዩ ተዋናይ እንድሆን ተደርጌያለሁ ሲልም ጨምሮ አጋልጦዋል፡፡

ዶክተር ባርናባስ የተባለው የህወሀት ባለስልጣን የተሰጠውን ትዕዛዝ ካስፈጸመ በሁዋላ ተጠያቂ እንዳይሆንና እንዳይወነጀል መለስ ዜናዊ በአንድ ሌሊት ከፌዴራል ጉዳዮች ሚኒስትር ደኤታነት ወደ ትግራይ ክልል የጤና ቢሮ ኃላፊነት እንዳዛወረው ገልፆ ሻለቃ ገብረ እግዚአብሄር የተባለውም የሌ/ኮ/ል ማዕረግ ተሰጥቶት ወደ ሰሜን እዝ እንዲዛወር ሲደረግ እኔ የክልሉ ፕሬዝዳንትና የጋህዴን ሊቀመንበር ሆኜ ልሸም ችያለሁ ብሎዋል፡፡

አቶ ኦኬሎ አኩዋይ በድርጊቱ ባለማመኑ ሲከራከርና ሲጨቃጨቅ የነበረ መሆኑን የጠቀሰው ይሄው ግለሰብ መለስ ዜናዊ በወታደራዊ ራዲዮ ባስተላለፈው ትዕዛዝ መሰረት እንዲያዝ እና እንዲታሰር ሲፈለግ ሌሊት ባልታወቀ ሁኔታ ከሀገር ጠፍቶ ማምለጡንም ለተሰብሳቢዎቹ አብራርቶዋል፡፡

በዚያን ወቅት በጅምላ ጭፍጨፋው ላይ ሲሳተፉ የነበሩ ወታደሮች እንዳይጠየቁና ብሎም ምስጢር እንዳያወጡ ወደ ተለያዩ የጦር ክፍሎች እንዲበተኑ ሲደረግ በምንም አይነት ተግባር ላይ ያልተሳተፉ 12 የመከላከያ ተራ ወታደሮችን ከየት እንዳመጡዋቸው ሳይታወቅ ጭፍጨፋውን የፈጸሙ ናቸው በሚል በእድሜ ልክ እስራት እንዲቀጡ መደረጉንም ጨምሮ የደረሰን ዘገባ አጋልጦዋል፡፡

ለእረፍት በአጋጣሚ በጋምቤላ ከተማ እንደነበሩ የተነገረላቸው እነዚህ 12 የመከላከያ ወታደሮች ከያሉበት ተይዘው ለፕሮፓጋንዳ ፍጆታ ተብሎ በመለስ ዜናዊ ትዕዛዝ ፍርድ ቤት እንዲቀርቡ ከመደረጉም በተጨማሪ በሚዲያ ሰፊ ሽፋን ተሰጥቶት ሲዘገብ እንደነበር ያስታወሰው የደረሰን ዘገባ በእድሜ ልክ እስራት ተወስኖባቸው ዛሬ በዝዋይ እስር ቤት ውስጥ ታጉረው እንደሚገኙም ገልፆዋል፡፡

በ1996 ዓ.ም የሚገደሉትን የአኙዋክ ተወላጅ ስም ዝርዝር ይዘህ ስለተገኘህ በእልቂቱ ተጠያቂ ልትሆን አትችልም ወይ? ተብሎ በገምጋሚዎቹ የተጠየቀው ኡሞድ ኦቦንግ ድርጊቱን ፈጽሜያለሁ ነገር ግን ትዕዛዝ ተሰጥቶኝ ነው ሲል ማመኑንም ከደረሰን ዘገባ ለማወቅ ተችሎዋል፡፡

ኡሞድ ሲያብራራም በእርግጥ የስም ዝርዝሮቹን ለመከላከያ ከፍተኛ መኮንኑ እና ለዶክተር ባርናባስ ሰጥቻለሁ ነገር ግን እኔ አልገደልኩም ገዳዩ ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ ናቸው ምክንያቱም አኙዋኮች እንዲገደሉ ትዕዛዝ የሰጡና የወሰኑት እርሳቸው ብቻ ናቸው ስለዚህ እኔ በጉዳዩ የምጠየቅ ከሆነ እርሳቸውም መጠየቅ አለባቸው ሲል ገልፆዋል፡፡

ኡሞድ ኡቦንግ ይህንን ምስጢር እንዳጋለጠ ከጥቂት ሰዓት በሁዋላ ከክልሉ ፕሬዝዳንትነት እና ከጋህዴን ሊቀመንበርነት እንዲሳ ተብሎ የተወሰነ ቢሆንም ከ24 ሰዓት ቆይታ በሁዋላ ከመለስ ዜናዊ በመጣ ትዕዛዝ ተመልሶ በክልሉ ፕሬዝዳንትነት እንዲቀመጥና ከፓርቲው ሊቀመንበርነት ተነስቶ በምክትል ሊቀመንበርነት ለስድስት ወር ብቻ እንዲሰራ መወሰኑን ከስፍራው የደረሰን ዘገባ አብራርቶዋል፡፡

በአሁኑ ሰዓት የክልሉ ፕሬዝዳንት ኡሞድ ኡቦንግ በደህንነት ልዩ ክትትል እና ጥበቃ ከቢሮው ወደ ቤት ከቤት ወደ ቢሮው ብቻ ተወስኖ በቁም እስር ላይ እንደሚገኝ ከስፍራው የደረሰን ዘገባ አብራርቶዋል::

ከስልጣኑ ተባርሮ የነበረው ኡሞድ ኡቦንግ በ24 ሰዓት ባልሞላ ግዜ ወደ ነበረበት ርዕሰ መስተዳድር ስልጣኑ የተመለሰው በመለስ ዜናዊ ትዕዛዝ መሆኑን የጠቆሙት ምንጮቹ ጉዳዩ በዓለም አቀፍ ፍርድ ቤት የተያዘ በመሆኑ ይሄ ጉዳይ እንዳይቀሰቀስ እና ምስጢሩ ተዳፍኖ እንዲቀር ለማድረግ ታስቦ መሆኑንም ምንጮቹ አክለው ገልፀዋል::

ይሁን እንጂ ሰሞኑን በጋምቤላ ክልል ባለስልጣናት ተጋልጦ የወጣው አስገራሚ ጉዳይ ተዳፍኖ እንዲቀር ቢታሰብም የዓለም አቀፉ የሰብአዊ መብት ተቆርቋሪ ድርጅት ግን እንደገና በስፋት ግምገማው መቀጠል እና ይፋ መውጣት አለበት ሲል ጥሪ አቅርቦዋል::

የአለም አቀፉ የሰብአዊ መብት ተመልካች በ1998 ዓ.ም ባወጣው ሪፖርት የኢትዮጵያ ወታደሮች በነሐሴ ወር 1996 ዓ.ም በአኙዋክ ብሔር ተወላጆች ላይ እጅግ አሰቃቂ የጅምላ ጭፍጨፋ ያደረጉ መሆኑንና በሴቶች ላይ አስገድዶ የመድፈር ድርጊት የፈጸሙ በመሆኑ እነ መለስ ዜናዊን ተጠያቂ እንዲሆኑ በማለት ክስ አቅርቦ የነበረ ቢሆንም እነ መለስ ዜናዊ ግን በወቅቱ የተፈጸመውን የጅምላ ጭፍጨፋ ሽፋፍነው ማለፋቸው ይታወሳል::

ሙስናን በተመለከተ በተነሳው በዚሁ ግምገማም ላይ በጋምቤላ ክልል ውስጥ ለም የእርሻ መሬት ለመለስ ዜናዊ ባለቤት አዜብ መስፍን ሰጥቻለሁ እስዋም በሌላ ሰው ስም እየሰራች ነው በማለት ያጋለጠ ሲሆን ለባዕዳን ዜጎችም  መሬት በርካሽ እንዳድል የነመለስ እጅ አለበት በማለት አጋልጦዋል::

ባለፈው ወር ካራትሪ የተባለው የህንድ ኩባንያና ሌሎችም ኢንቨስተሮች መሬቱን ለእርሻ ሲመሩ በአካባቢው ለዘመናት የኖሩትን ዜጎች እንዲፈናቀሉ የተደረገ ሲሆን ለመሬታቸው ካሳ ሳይከፈላቸው ባዶ እጃቸውን እንዲባረሩ መደረጋቸውን የጠቆመው የውስጥ አዋቂ ምንጮች ገለፃ ኡቦንግም ከፌዴራል ባለስልጣናት ጋር በመመሳጠር ከባለሀብቶቹ ላይ በሚሊዮን የሚቆጠር ብር መውሰዱን አጋልጠዋል::

ይህ ግለሰብ ይላሉ ውስጥ አዋቂ ምንጮቹ ይህ ግለሰብ በአዲስ አበባ ሁለት እጅግ ዘመናዊ ቪላዎችን አሰርቶ ያስቀመጠ ሲሆን የንግድ መኪኖችም ብዙ እንዳሉትና በወንድሙ ስምም በሚሊዮን የሚቆጠር ብር በባንክ ማከማቸቱን ገልፀዋል::

ይህ በእንዲህ እንዳለ በጋምቤላ እየተፈጸመ ያለው ዜጎችን የማፈናቀል ስራ በስፋት እየቀጠለ መሆኑ ከስፍራው የደረሰን ዘገባ አጋለጠ::ሰሞኑን የወያኔ ቡድን አስገዳጅ የሰፈራ ፖሊሲ በመከተል ለዘመናት ከኖሩበት ሀገር ...... እትብታቸው ከተቀበረበት ቀዬ.....እያፈናቀለ መሬታቸውን ለባዕዳን ባለሀብቶች ከመቸብቸቡም በላይ ነዋሪዎቹን ሰፈራ በሚል ምክንያት ወደ በረሀ እያጉዋጉዋዘ መሆኑ ታወቀ::

በቅርቡ በሰፈራ ስም በተደረገው የማፈናቀል ስራ ዋነኛ ተጠቂዎቹ የአኝዋክ ብሄር ተወላጅ መሆናቸውን የጠቆመው የደረሰን ዘገባ እነዚህ ዜጎች አርብቶ አደሮች በመሆናቸው ለም መሬት ላይ ሰፍረው በመኖር ላይ ቢሆኑም ወያኔ ግን አሁንም በመሳሪያ ኃይል በማስፈራራት እና በማፈስ ወደ በረሀ ወስዶ እየጣላቸው መሆኑ ታውቆዋል፡፡

በተመሳሳይ ዜና  የአፋር ክልል ባለስልጣናትን ሲፈራና ሲያከብር የነበረው የወያነው መሪ መለስ ዜናዊ ሰሞኑን ግን ባለስልጣናቱን በሙስና ሰበብ እየመነጠረ ለእስር እየዳረጋቸው መሆኑን ከስፍራው የደረሰን ዘገባ ገልፆዋል፡፡

በክልላችን የመወሰን መብቱ የእኛ እንጂ የመለስ አይደለም ሲሉ ሲፎክሩ የነበሩት የአፋር ክልል ባለስልጣናት ለስብሰባ ተብሎ አዲስ አበባ በተጠሩበት ወቅት ድንገት በደህንነት ሰራተኞች ተይዘው ለእስር መዳረጋቸውን ከአይን እማኞች ለማረጋገጥ ተችሎዋል፡፡

በዚሁ ተጠራ በተባለ የክልል ባለስልጣናት ስብሰባ ላይ የተገኙ ሶስት የአፋር ባለስልጣናት ወደ ስበሰባ አዳራሹ ሊገቡ ሲሉ ድንገት ከበሩ ላይ ተይዘው ማዕከላዊ እስር ቤት የገቡ ሲሆን ብዙዎቹ ደግሞ ከስልጣናቸው እንደተባረሩም ለማወቅ ተችሎዋል፡፡

የአፋር ክልል የፋይናንስ ኃላፊ እና የቤቶች ኤጀንሲ ኃላፊ የነበሩት ሁለት ባለስልጣናት ከስብሰባ አዳራሹ በር ላይ ተይዘው ሲታሰሩ አንደኛው ደግሞ ከክልሉ ተጠልፎ መጥቶ ለእስር እንደተዳረገ የደረሰን ዘገባ አስታውቆዋል፡፡

በድርጊቱ የተበሳጩ የክልሉ የወረዳና የዞን አስተዳዳሪዎች በገዛ ፍቃዳቸው ስራቸውንና ስልጣናቸውን እንቃለን በማለት ያስታወቁ ቢሆንም ለመለስ ቅርብና ቀኝ እጅ በሆነው እስማኤል አለሴሮ በኩል በመለማመጥ ቦታቸው ላይ እንዲመለሱ መደረጉን ከስፍራው የደረሰን ዘገባ ጨምሮ ገልፆዋል፡፡

ከዚህ ቀደም የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የአሳይታ ዞን የፖሊስ አዛዥ የነበረውን  ግለሰብ ለፍርድ እንዲቀርብ ተደጋጋሚ ግዜ ማዘዣና መጥሪያ ቢልክም እኛ የምንዳኘው በራሳችን እንጂ በማንም ወያኔ ሰራሽ ሰዎች አይደለም በማለት ምላሽ መስጠቱን ተከትሎ ባለፈው ሳምንት ድንገት በደህንነቶች ታፍኖ ወደ አዲስ አበባ ማዕከላዊ እስር ቤት ሊገባ እንደቻለም የደረሰን ዘገባ አብራርቶዋል፡፡

ከ18 ዓመት በላይ የአፋር ክልል ፕሬዝዳንት ሆኖ የተቀመጠው እስማኤል አሊሴሮ የሀገር እና የህዝብን ሀብት እየዘረፈ በሀገሪቱ አሉ የተባሉ ሀብታሞች በላይ ከፍተኛ ሀብት ያከማቸ ቢሆንም ሰሞኑን በተደረገ የክልሉ ባለስልጣናት ግምገማ ላይ ብዙ ትችት እና ውንጀላ ቢቀርብበትም የክልሉን ፖለቲካ  ያረጋጋል በሚል በከባድ ማስጠንቀቂያ ብቻ እንዲታለፍ መደረጉንም ከስፍራው የደረሰን ዘገባ አብራርቶዋል፡፡

በመጨረሻም የወያኔ ቡድን ሀገሪቱ በእድገት እየተመነጠቀች ነው እያለ የዓለም ህብረተሰብን ለማታለል ባዶ ፕሮፓጋንዳ እየነዛ ቢሆንም አሁን ባለው ተጨባጭ እውነታ ግን ዜጎች ከፍተኛ ችግር ላይ መውደቃቸው ተረጋገጠ፡፡

በአዲስ አበባ ከተማ የኑሮው ውድነት በመክፋቱ ርሀብ ተከስቶ ቁጥራቸው የበዛ ዜጎች በየጎዳናው ላይ ወድቀው መታየት የተጀመረ ሲሆን ተማሪዎችም የሚቀምሱት እያጡ ትምህርት እስከማቁዋረጥ መድረሳቸውን ከተለያዩ አካባቢዎች የሚደርሰን ጥቆማ ያስረዳል።

ሰሞኑን ተዘዋዋሪ ዘጋቢያችን በአዲስ አበባ ከተማ ባሉ ትምህርት ቤቶች እንደተመለከተው ከሆነ ሙሉ ቀን የሚያስተምሩ የመንግስት ትምህርት ቤቶች ውስጥ ተማሪዎች ቁጥራቸው እያነሰ መምጣቱንና ቀኑን ሙሉ የሚውሉትም የሚቀምሱት በማጣታቸው በግቢው ውስጥ ወድቀው መመልከቱን ዘጋቢችን ገልፆዋል።

በተለይ ከተመሰረተ አራት ዓመት የሆነው በጃፓን መንግስት ድጋፍ የተሰራው የህዳሴ አንደኛና መለስተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች በርሀብ ምክንያት እየወደቁ ለከፋ ችግር ከመዳረጋቸውም በተጨማሪ ትምህርታቸውን መከታተል እንዳልቻሉም አረጋግጦዋል።

ከቤተሰቦቻቸው ምሳ ተቁዋጥሮላቸው የማይመጡ ተማሪዎች የዚህ ሰለባ ዋነኛ ተጠቂ መሆናቸውን የጠቆመው ዘጋቢያችን ይህንን ችግር ለመቅረፍ በትምህርት ቤቱ የሚያስተምሩ መምህራን ከሚከፈላቸው ወርሀዊ ክፍያ ላይ እየቀነሱ ምሳ ለማቅረብ ቢሞክሩም ከተማሪዎቹ ቁጥር መብዛት የተነሳ ሁሉንም ለማዳረስ እንዳልቻሉ ዘጋቢያችን ገልፆዋል።

ዛሬ መላው የሀገሪቱ ዜጎች በኑሮ ውድነት ውስጥ ተዘፍቀው በቀን አንዴ መብላት ተስኖዋቸው ባሉበት ወቅት ለልጆቻቸው ምሳ ሊቋጥሩ የሚችሉት በመጥፋቱ ባዶ እጃቸውን እንዲሄዱ በመደረጉ ብዙዎቹ በትምህርት ቤት ውስጥ እየወደቁ እንደሚገኙም ለማየት ተችሎዋል።

በአሁኑ ሰዓት እጅግ ቁጥራቸው የበዙ የሀገሪቱ ዜጎች በከፋ ችግር እና ርሀብ ላይ የሚገኙ ሲሆን ወያኔ ግን በሀገሪቱ ጥጋብ እንደሞላ አድርጎ ፕሮፓጋንዳ መንዛቱ አሳፋሪና ለዜጎች ደንታ የሌለው መሆኑን ያሳያል ሲሉም የትምህርት ቤቱ መመህራኖች እያለቀሱ በቁጭት ሲናገሩ መደመጣቸውን ዘጋቢያችን አስረድቶዋል።